# በአሁኑ ወቅት የዚያን ትውልድ የትግል ታሪካ የማንቋሸሽና የመከለሱ ዘመቻ ለምን አስፈለገ?

ሰሞኑን የዋለልኝ መኮንንን ታሪክ የማጥቂር ዘመቻው ተጧጡፏል። የአማራ ሕዝብ ጠላትም እየተደረገ እየቀረበ ነው። የማርታ መብራቱም የትግል ታሪክ በኤርትራዊነቷ የነሻቢያ መሣሪያ በመሆን እነዋለልኝን እንዳነሆለለች ተደርጎ የኢትዮጵያ የተማሪዎች እንቅስቃሴም የዘረኞች መጠቀሚያ ሆኖ እንደነበር የሚሰብኩን ሊቃውንት በየመድረኩ ብቅ ብለዋል። ዕውነትና ንጋት እያደር ይጠራል ነውና የዚያን ትውልድ ትግል ለመሆኑ የዛሬውን የዘረኝነት መነጽር ተላብሶ ለመመልከት መሞከር ስህተት አይሆንም ወይ? የወያኔው መርዘኛ የዘረኝነት ሥርዓት ተንሠራፍቶ ባለበት በዚህች ቀውጢ ጊዜ ለመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ እኩለነት መስዋዕትነት ከፍለው ያለፉ እኒያ ታጋዮችን አንስቶ መውቀጡ፤ የሙት ወቃሽ መሆኑ የታጋዩን ጎራ ከመከፋፈል ውጪ የሚፈይደውስ ምንድር ነው? የሚዘምተውስ ማነው?

ያ ትውልድ ከተመክሮ ማነስ በትግል ውስጥ ብዙ ስህተቶችን ፈጽሞአል።
ጠላትም ሆነ ወዳጅ የማይክደው ሀቅ ግን ያ ትውልድ በአማራው፣ በትግሬው ፣ በኦሮሞው ...ወዘተ. ሕዝብ ላይ አልዘመተም። መሬት ላራሹ! የድሃ ልጅ ይማር! የዴሞክራሲያዊ መብት ለሁሉም! ለኃይማኖት እኩልነት ለሠራተኛው መብት ታገለ አታገለ እንጂ። ከሁሉም በላይ ግን በኢትዮጵያዊነት ላይ ከማንም ሰይጣን ጋር አልተደራደረም።

ለምሳሌ የወያኔ አንዱ መሪ የነበረው ገብሩ አሥራት በቅርቡ በጻፈው መጽሐፍ ገጽ 54 ላይ እንዲህ ይላል

> *"ኢሕአፓ በፕሮግራሙ ውስጥ የኢርትራ ጥያቄ በሰላማዊ መንገድ መፈታት እንዳለበት ከመግለጹም በላይ በዴሞክራሲያ በሚያወጣቸው መግለጫዎች ከሰላማዊ ድርድር ውጭ ሌላ መፍትሔ ማፈላለግ ዕልቂት እንጂ ሌላ ውጤት እንደማይኖረውም በተደጋጋሚ ይገልጽ ነበር። ይህ የኢሕአፓ አቋም የኤርትራን ድርጅቶች የሚያረካ አልነበረም። የኤርትራ ድርጅቶች ኢሕአፓ በሁለት ጉዳዮች ላይ ጠንካራ አቋም እንዲኖረው ይፈልጉ ነበር። አንደኛው አቋም የኤርትራ ጥያቄ የቅኝ ግዛት መሆኑና ቅኝ ገዥዋም ኢትዮጵያ እንደሆነች መቀበል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ጥያቄው በኤርትራ ነጻነት መፈታት እንዳለበት መቀበል ነበር። እነዚህን ሁለት አቋሞች ከኢሕአፓ ሊያገኙ ባለመቻላቸውም የኤርትራ ድርጅቶች በኢሕአፓ ላይ ከፍተኛ ጥርጣሬና ጥላቻ ነበራቸው...."*

ወረድ ብሎ በዚሁ መጽሐፍ ገጽ 135 ላይ ለምሳሌ ከኢሕአሠ ተገንጥሎ ወደ ወያኔ የተቀላቀለው ጦር (እነ ታምራት ለይኔ፣ ሕላዊ ዮሴፍ፣ ታደሰ ካሣ፣ ያሬድ ጥበቡ (ጀቤሳ)፣ ኃይሌ ጥላሁን፣ በረከት ስምዖንና አዲሱ ለገሠ ኢሕዴን ብለው በሰየሙት ድርጅት አማካይነት የኤርትራ ጥያቄ የቅኝ ግዛት ነው ብለው ተቀብለዋል ብሎ ያቀርባል።

የአሲምባ ድሕረ-ገጽ ዝግጅት ክፍል